# ዝክረ አድዋ በኪነጥበብ መወድስ

ዳንኤል አበራ (danlinet@yahoo.com)

## ቅድመ አድዋ ትውስታ

ኢትዮጵያ ከዘመነ መሳፍንት ተላቃ አንጻራዊም ቢሆን ወደ ተረጋጋ ማእከላዊ አስተዳደር የተሸጋገረችበት ዘመን። አባ ዳኘውም እምዬም እየተባሉ ሲጠሩ የነበሩት አፄ ምኒልክ ስልጣን ያደራጁበት እና ኢትዮጵያን ያሰሱ አውሮፓውያንን ባላሰለሰ የመሳሪያ ስጦታም ግዢም ጥያቄ የወተወቱበት ዘመን፤ ኋላም ተክለ ጻድቅ መኩሪያ እንደጻፉልን «ባመጣው ወጨፎ ባመጣው እርሳስ ተፈጠመ ጣሊያን አበሻ እንዳይደርስ» ከተባለበት የጣሊያን መንግሥት ጭምር የመሣሪያ ስጦታ ተረከበው ምኒልክ ጦራቸውን ያደራጁበት ዘመን፤ አውሮፓውያን አህጉራትን እንደ ቅርጫ ስጋ የተከፋፈሉበት ዘመን።[1] አፍሪካም፣ ኢትዮጵያም የዚህ እጣ ፈንታ ተቋዳሽ እንዲሆኑ በዝግ ተወስኖ ለአፄ ምኒልክና መንግስታቸው መልእክት የተነገረበት ዘመን፤ አፄ ምኒልክም መልእክቱን ሰምተው እግዜር ይስጥልኝ ውሳኔያችሁን አልቀበልም ያሉበት፣ የጦርነትም ስጋት ያንዣበበት ዘመን ነበር ዘመኑ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ከህዳር በሽታ ያገገመበት፤ እውነት መሆኑን ያላረጋገጥኩት ግን ጣሊያኖች ባመጧቸው የታመሙ ከብቶች የኢትዮጵያ ከብቶች ያለቁበት፣ ረሃብ ነግሶ ህዝቡንም ደቋቁሶ መንሰራራት እየታየ ያለበት ወቅት ነበር ዘመኑ።

ሲቻል በውድ ሳይቻል በግድ ጣሊያን ኢትዮጵያን ልትውጥ የተዘጋጀችበት ነበር ዘመኑ። ካውንት አንቶኔሊ በውጫሌ ውል መፍረስ ሳቢያ የምኒልክን ጉባኤ ረግጦ ይለያል ዘንድሮ የኢትዮጵያ ኑሮን አቅራርቶ በእትጌ ጣይቱም ባይገርምህ ላፈሩ-ላገሩ ሆዱን ለጠጠር ግንባሩን ለጥይት የማይሰጥ ሰው እዚህ ያለ እንዳይመስልህ በሚል ምላሽ የተለያዩበት ነበር ወቅቱ የዛሬ መቶ አስራ አራት አመት።

## አፈር - መሬት - ሀገር - እትብት - ህይወት - ሞት

ሲጀመር የአፈር ሀገር ተምሳሌት በኢትዮጵያውያን ህይወት ውስጥ ሁነኛ ስፍራ አለው። ጣልያኖችም ያንን ያውቃሉ እንደ ከበደ ሚካኤሉ "ቹሊ" አባባል ከሆነ። አፈራችሁ እትብታችሁ የተቀበረበት ጎጆዋችሁ ወጋችሁ ሃይል ስለሌላችሁ ይነጠቃል ብሎ ነው የሚያቅራራው።

የምትኮሩበት እንግዲህ እናንተ
እኔ እዚህ ተወለድሁ አባቴ እዚያ ሞተ፣
ካያት ከቅድመ አያት የመጣው ርስቴ
የሠራሁት ጎጆ ያቆምሁት ቤቴ
ለምን ተነከቶብኝ በማለት ብቻ ነው
ነገር ግን ነገሩን ስታመዛዝነው
ሃይለኛ ይሔዳል ያስገብራል የትም
መሬት የሁሉ ናት ባለቤት የላትም[2]

አፈር-መሬት ሃገር ነች እናት ነች ይለናል የሐዲስ ንጋት የኪነጥበበ መድረኩ ባዩ በየነ (2000፡135-7) በ«**ፍቅር ወይስ ቂጣ**» ግጥሙ ያንቺ ፍቅር አያጠግበኝም ኩርማን እየበላሁ የጠኔ ህይወት እየገፋሁ ይል ይማረርና መለስ ብሎ ደግሞ እናትነቷ ቢጠናበት

ዳሩ አንቺ አይደለሽ አመዳሙ እኔ ነኝ፤
ሥጋሽ አልቆ ፈርስሽ ላይ የጸነሰኝ፤
ያን ሁሉ ወፈ-ሰማይ ግብር ያበላ እጅሽ
ሲመገመግ ቢውል የማይደርቀው ጡትሽ
ምነዋ እኔ ስወለድ ነጠፈ?[3]
...

እያለ ይጠይቃል ምስጢሩ ቢገለጽለት። ሲያሰኘውም «**አበሳሽን እኖራለሁ**» ይላታል ስደት ሆኖ የሃገር የአፈር ናፍቆቱ ውል ቢልበት፤

እንደዛሬው በልቶ ማደር ሳይናፈቅ፣
ሞት ሳይረከስ ፍቅር ሳያልቅ፤
የግሬን አፈር ጠርጌ ሳልሰደድ ሳልርቅሽ፣
አይደለም በስጋዬ በመንፈሴ ሳልለይሽ፤[4]

የአፈር ሃገር ተምሳሌትነት በሐዲስ ንጋት የኪነጥበበ መድረኩ የግጥምና አጫጭር ታሪኮች መድበል «**አቦል**» አይነተኛ ቦታ ይዟል። ታምራት ገበየሁ (2000፡202)«**የማስቸግራችሁ**» እያለ የሃገሬን አፈሯን ዘግናችሁ ትቢያዋን ቋጥራችሁ አምጡልኝ ይለናል።

ሀገሬ ስትገቡ፤
ኢትዮጵያ ስትዘልቁ
...
ብዬም አልላችሁ
ግን አለ አንድ ነገር፣
የማስቸግራችሁ
አፈሯን ዘግናችሁ
ትቢያዋን ቋጥራችሁ
አምጡልኝ ሃገሬን
እናት ኢትዮጵያዬን።[5]

ዮሴፍ ያእቆብም ቢሆን ነፍስ አፈር ነወይ? እያለ ትግያውን ያሰየናል «**ነፍስ**» በተሰኘ ግጥሙ።

አፈር ነህ ይሉኛል
ከቶ አፈር ነኝ ወይ?
እንደ ጥላ ኮብላይ
ጠፊ ከምድር ላይ...
እኔ አይደለሁ አፈር
ጥርኝ ጭብጥ ነገር...
እሱኛው ነው፣ እሱኛው ነው በድን...[6]

ይህ ያፈር ያገር ነገራችን የዘመናችን ተዋነይን በ"ዕውቀቱ ስዩም"ንም አስደምሞት አስገርሞት ይሆን "**አፈር እንቅቅልህ**" ያለው።[7]

አፈር፦
በምድሬ ሥር፦ ማፍሪያ
በጥፍሬ ሥር፦ ማፈሪያ
በውኃ የማባርረው
በደሜ የማስከብረው
በልቤ ስይዘው፣ የሚያሽልመኝ
በልብሴ ስይዘው የሚያስቀይመኝ

የታሰበውም አልቀረ ጣሊያን በባራቲየሪ ፊት አውራሪነት በጄኔራሎቹ የሚታዘዘውን ጦሩን ክተት ብሎ አድዋ ደረሰ። ይኼኔ ነበር ዝነኛው የምኒልክ አዋጅ የተነገረው። የህዝቤን መነሳቀል የከብቱን ማለቅ አይቼ ዝም ብለው እንደ ፍልፈል ምድር እየቆፈረ መሬታችንን ያዘ። ያልቻልህ በጸሎትህ የቻልህ በጉልበትህ እርዳኝ ወሳልተህ የቀረህ እንደሆነ ማርያም ምስከሬ ናት አልምርህም። ህዝቡም ይህን የአዋጅ ጥሪውን ሰምቶ ክተት አለ ወደ ጦሩ አውድማ ወደ አድዋ። ኪነጥበብ ህዝቡን እንዲህ ታወድሰዋለች።[8]

### ወደ ጦር ሜዳ

በመደቡ ራስጌ ሰቅሎ ያኖረውን
አወላልቆ ጠርጎ ናስማስር ብረቱን
ወልውሎ እንደገና አስማምቶ ገጣጥሞ
ጥይቱን አጉርሶ ቃታውን ለጉሞ
በረዥም መቀነት ሸብ አርጎ ወገቡን
በመቀነቱ ላይ ደርቦ ዝናሩን
ሚስትና ልጆቹን ስሞ ተሰናብቶ
ሄደ ገሰገሰ የባላገር ስንቁን በስልቻ አንግቶ

## አድዋ

ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ በአስገራሚ ሁኔታ ጦርነቱ እንደ ማንኛውም ጦርነት የሰው ህይወት ተገብሮበት ተጠናቀቀ አሸናፊም ተሸናፊም ተለየ። በዊኪፔዲያ እንደተዘገበው ከጣሊያኖች ወገን 7000 ከኢትዮጵያውያን ደግሞ 4500 ያህል ሰዎች ተሰውተዋል። 3000 ጣሊያኖችም ተማርከዋል። ባንዳዎችም በዘመኑ አጠራር አስካሪዎችም እጃቸው ተቆርጧል ይባላል። ሆኖም አድዋን ልዩ የሚያደርገው ወሳኙ ፍልሚያ አድዋ ላይ መካሄዱም አይደለም። ርግጥ ነው ጦርነቱ የኢትዮጵያንም የታሪክ አቅጣጫ ቀይሮአል። እሱን አልሄድበትም። ጦርነቱ -ድሉ ተስፋ ሰጪነቱ፤ ጦርነቱ ድሉ - ተምሳሌትነቱ ነው። ሲያንስ የተገፉ ህዝቦች - ጥቁሮች በኃይለኛ ህዝቦች - በነጮች ላይ ያገኙት ድል ስለሆነ ነው። ሲበዛ ደግሞ ደካሞች በትእቢተኞች ላይ ያሰገኙት ድል ምሳሌነቱ ነው ከበደ ሚካኤል በ "**እሮሮ**" እንደተቀኙት።[9]

እግዜር የሰውን ልጅ እንፍጠር ሲል ሠራ፣
ፋሺስቱ ብልህ ግን አድርጎ ምርመራ
የሃያኛው ዘመን አዲሱ ፈላስፋ
አለና ተነሳ የሰው ዘር እናጥፋ
...
ሁሉም በየተራ ቀን ይጎድልበታል፣
አሸናፊ ደግሞ አንድ ቀን ይረታል።
...
ትዕቢት ትመጣለች ውርደት አስከትላ
የተመካ ሁሉ ይጠፋል በኋላ።

የአድዋ እለት ወራሪው ጦር ቀን ጎደለበት። አሸናፊው ትምክህተኛው ተዋረደ ተሸነፈ። ኢትዮጵያውያን አድዋን እንዴት ዘከሩት አወደሱት የሚለውን የሙቶ አስራ አራት አመት ጥያቄ ገረፍ ገረፍ አድርጌ ልለፍ።

## ድህረ አድዋ

አድዋ በድህረ ጦርነቱ ዘመን በተለያየ መንገድ ተዘክሯል። መሆን የማይገባውም ነገር ሆኗል። አድዋ አድዋነቱ ተምሳሌትነቱ ግን አሁንም በኢትዮጵያውያን ልብ እንዳለ ነው። (ይህ የድህረ አድዋ ዝክር ሃሳብ መሰረት ያደረገው ቢንያም ወልደገብርኤል በ1997 ኢ.ም. በታሪክ ትምህርት ለማስተር ዲግሪው ያቀረበውን ጥናት ነው።)

አንዱ ድህረ አድዋ መወድስ እስካሁንም ድረስ የሚታወስ እና ኪናዊ ውበት የተላበሰ የቀኝ ጌታ ዮፍታሄ ንጉሴ ግጥም ነው።[10] አድዋን በኢትዮጵያ ህዝብ ትብብር ማሸነፋችንን አጉልቶበታል።

አጥንቱን ልልቀመው መቃብር ቆፍሬ
ጐበናን ከሸዋ አሉላን ከትግሬ
ስመኝ አድሬያለሁ ትላንትና ዛሬ
አሉላን ለጥይት ጐበናን ለጭሬ
ተሰበሰቡና ተማማሉ መሃላ
ጐበና ሴት ልጁን ሊያስተምር ፈረስ
አሉላ ሴት ልጁን ጥይት ሊያስተኩስ
...
ትምህርት እንዲሰፋ አገር እንዲጠና
አራቱ ጉባኤ ይሁኑልንና
መኮንን ደረሶ አሉላ ጎበና
አገራችን ትማር አሁን እንደገና

## የአድዋ መቶኛ አመት

የአድዋ ምእት አመት መከበር እንደነበረበት ሳይከበር ያለፈ ያመለጠ አጋጣሚ ነው። እንደ ቢኒያም አገላለጽ ከሆነ ችግሩ የተፈጠረው በአሉን ለማክበር የተቋቋሙት ሶስቱ የኢትዮጵያ ምርምር እና ጥናት ተቋም ኮሚቴ፣ ኢህአዴግ ያቋቋመው ብሔራዊ ግብረ ሃይል እንዲሁም በትግራይ ክልል የተቋቋመው ግብረ ሃይል እርስ በርስ ባለመስማማታቸው ሲሆን የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶችም ጫናም ጭምር ነበረበት። አይነተኛ ምክንያቶቹ የትግራይ ክልል በአሉ ሙሉ በሙሉ በትግራይ መከበር አለበት በማለቱ የፖለቲካ ድርጅቶችም በተለይ ምኒልክ እና አድዋ ተነጣጥለው እንዲታዩ ያደረጉት ግፊት በአሉን የጨረባ ተዝካር አድርጎታል።

ያም ሆኖ አንዳንድ ተጠቃሽ ኪነጥበባዊ ፍሬዎች ነበሩ። የታምራት ገበየሁ ውጫሌ 17 ትያትር የአባተ መኩሪያ ከአራት ሺ ሰዎች በላይ ያሳተፈ «ወደ አድዋ ጦርነት ጉዞ» ፊልም እና በተሻገር ፍሬው የቀረበው "አድዋ" ግጥም ዋናዎቹ ናቸው። የምርም የተሻገር ፍሬው አድዋ ግጥም ከቋንቋው ምጥቀት ከሃሳቡ ብስለት እና ምሉእነት ከኪናዊው ውበት አንጻር ሽልማትም ሲያንሰው ነው። ከነበረበት የ sera ቅርጽ ወደፊደል መልሼዋለሁ። ሙሉ ግጥሙን እነሆ።[11]

**አድዋ**[1]

አድዋ! አንቺ የዝና አጥናፍ
ህዝቦች እፍ ያሉሽ ቁጣ የነበልባል እቶን ጫፍ
አጹብ ክስተት - ደቂቅ ረቂቅ - ምጡቅ መሊቅ
ትንግርት እውነት - ታምር ሁነት - የብርቅ ብርቅ
የድንቅ ድንቅ
ኬላ ድንበር - አድማስ ሰበር - የቅርብ ሩቅ
ለትንግርትሽ ብቻ መጥኔ
ለሰጠሽው ፍትህ መጠን፣ ለፍርድሽ ሚዛን ብያኔ
ለንግርትሽ ስነ ውብት፣ ለታሪክሽ ምስጢር ቅኔ።

መገን! ለሁነትሽ ታምር ሁነት
አቤት! ለመከዳሽ ክቡር ክብረት
ለዙፋንሽ ሰብእና፣ ለሰብእናው ልእልና
ለምጥቀቱ ምጡቅ ምጥቀት
መገን! ለቆምሽበት ጥቁር አፈር፣ ለበቀልሽበት ሰናይ አለት
የሰብእና ሀሌታ ጡብ መሰረቱ ላረፈበት
በአዳም እግሮች ለተሟሸው፣ ለኢትዮጵያ ጭንጫ መሬት
ታሪክ መሆንን ሆኖ እትብቱ ለወደቀበት
አቤት አድዋ!... አቤት...አቤት
መገን አድዋ! ላንቺስ መገን
እንደሞት ግርማ የገዘፍሽ፣ በኢምንትነት ማህፀን
እንደ ጀምበር የደመቅሽ በድድቅ ጨለማ ዳፈን
አልማዝ እንቁ - ጮራ ጨረር - ብርሃን መነን
መገን አድዋ! ላንቺስ መገን
ንግርትሽ በዘመን ዱካ፣ በታሪክ አሻራ ታየን።

የታሪክ ፋና ዱካው ሁሉን ችሎ መች ሊያሳፍረው
በምን ቀሰም፣ በምን ቀለም፣ በምን ብራና ሊከትበው
በምን አንደበት ሊደፍረው፣ በምን ቋንቋ ሊለፍፈው
አፍሪቃዊ ውስጣችንን በምን ብሩሹ ሊነድፈው
ሰዋዊ ምስጢራችንን በምን አቅሙ ሊገልጸው
እኛው ጮኸን ካልዘከርነው፣ አውጥተን ካልተናገርነው።

በወዲያኛው ምእት አመት፣ ያለምነው ህልማችን፣ ያኔ
በቅሌያችን ስውር ቋንቋ፣ በውስጣችን ስብእና የተሳለ ረቂቅ ቅኔ፤
የተረት አደባባዩ፣ የየጎጆው መህል ስብሳብ
ቋንቋ ነበር የሚሰማን፣ የሚነግረን አንዳች ንግርት
ሲያንጎራጉር የሚገባን፣ የወደፊት መጪ ክስተት።

አድዋም አደባባይሽ፣ ጭንጫ መሬትሽ ነዘረ
አውሎ ነፋስሽ ፈጠነ፣ ሰማይ ደግፎ ሾረ
በጀ ስውር ተጥመልምሎ፣ ትቢያ በተነ ናረ
አቧራ እያበራየ፣ በሹክሹክታ ተናገረ።

---

[1] ለዝክረ አድዋ መቶኛ አመት መታሰቢያ ተወዳድሮ በአአዩ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋምን ሽልማት ያስገኘ ግጥም

ምኒልክ ሲሞሽር አየ፣ በህልም ቀለም ተስሎ
ጎልያድን ሲገነድሰው፣ ህጻኑን ዳዊት ተመስሎ
ዳኛው ተቅበጠበጠ፣ ቸኮለ ተቁነጠነጠ
በአክናፍ እየከነፈ፣ አየሩን እየቀዘፈ
በአበው ራእይ አለፈ።

ንግርት ውነቱ ረቀቀ
ቀለም ስእሉ ደመቀ
አድዋ ፍቿሽ ምስጢሩ፣ የታምርሽ ቀን ራቀ
ያጨሽ ሃያል ብርሃን፣ ባንድ ወገን እየሠረቀ፤
እንደ ቦና ኮሾ ቅጠል
ኮኮቦች ሁሉ ረገፉ፣ ፈለኮች ሁሉ ወደቁ
ማሾዎች ሁሉ ወደሙ፣ ፋኖሶች ሁሉ ደቀቁ
አፍሪካን ጨለማ ዋጣት።

ያውሮፓ መንጋጋ ታየ፣ ስታዛጋ አፏን ከፍታ
ወስፋቷ ጨኸት አሰማ፣ የምግብ ያለህ ኡታ
አይኖቿ ተቁለጨለጩ፣ ጎመዠች አፍሪካን አይታ፤
ድግሷም ደርሶ ደረጀ፣ ጣሯም ሰማይ ጠቀሰ
ፋና ወጊው ቀሰሰ፣ መስቀል ሰላጢን ያዘ።
ምጻታዊ ምልኪ ታየ፣ አበው ድንገት ተሳቀቁ
ያንቀላፉ አራዊት ባነው፣ ከየጉድጓዳቸው ነቁ፤
የመቃብር አፎች ጮኸው፣ በሚርት ሳቅ አወኩ
ተራሮች ራዱ፣ ቀላያት ተናዱ፤ አድባራት ፈረሱ።

ንግርታችንን ሊፈታ፣ ድንገት ከች አለ እንግዳ
ያፍሪካን አፈር ረገጠ፣ ደግ መሳይ ዱብ እዳ፤
የይሁንታውም ሀቅ መልክ፣ የውስጡ ምስጢር ገበና
ያኳኋኑ አከያየን፣ ያፈጣጠሩ ቅኔ ቃና
አድሮ ታየ፣ ተከሰተ። ለካስ እሱስ
ቅዱስ እርኩስ፣ እርኩስ ቅዱስ
መልአክ ሰይጣን፣ መንታ መንታ ሰብእና
ባድማ ልብ፣ መካን ስሜት፣ ክፍት መቃብር ህሊና
የሌሊት ወፍ መካለቢያ፣ ያውሬ ማደሪያ ወና
በርግብ አካል ውስጥ ያለ ክፉ ነጣቂ ሲላ
በበግ ለምድ የተሸፈነ፣ ጨካኝ መሰሪ ተኩላ፣ ኖሯልና።

አውሮፓም ጭምብሏን ጥላ፣ ጥሩር ጋሻዋን ለበሰች
ክራንቻ ጥርሶቿ ታዩ፣ ጦር ነቀነቀች ሰበቀች፤
ሮማ ተቁነጠነጠች፣ ሴሰነች ተቅበጠበጠች
የትምክህት ቅፍለት ጭና፣ ባህር ውሃውን ናጠች።
(ምልኪው ደረሰ ተገለጠ።)

ምድርን የሚያናጉ፣ ረግጠው የሚቀርፉ መቶ ሺ ጫማዎች
አፍሪካን ረገጡ አሲዳም እግሮች፣ የጎልያድ ኮቴዎች
ግዙፍ ሸሆናዎች፣ የብረት ዱካዎች።

ቆሌ አድባሯም ባነነች ተዳረሰ የምጥ ሰአት
አድዋን ያጫት ታሪክ፣ በልፍኝ በጓዳው ሞሸራት፤

ምኒልክ ቁርጡን ነገረ፣ ምታ ነጋሪት አለ
ሰራዊቱ ከተተ፣ ኢትዮጲስ ነቀለ
ሞፈር ጣለ፣ ሰቀለ፣ ውሃ ቅል አንጠለጠለ፤
አበው ተነቃነቁ፤ ደወል መረዋው ተደወለ
አፍሪካዊና አውሮፓዊ አድዋ ላይ ተዋዋለ።

እኩይና ሰናይ በመስመር ላይ ቆሞ፣ ግንባር ተነጻጽሮ
ልሂቅና ደቂቅ፣ ግዙፍና ረቂቅ፣ ለየራስ ተጣምሮ
ተዋግኖ ተቧድኖ፣ ምሎ ተማምሎ፣ ምስጢር ተመሳጥሮ

ልቡን አንጠልጥሎ ነቅቶ እንደጠበቀ
ምጡን ተፈጠጣት ፍጻሜዋ ራቀ
በሞት ሽረት ትግል ሁከት በረከት።

ብርቱ ነው ሁከቱ፣ ከቶ እማይገለጥ በቋንቋ በቃላት
ታሪክ ድርሳን መሀል አልፏልፎ የሚገኝ እጹብ ድንቅ ክስተት።
ልቦናን የሚንድ፣ ህሊናን የሚያርድ፣ እምነት የሚያጣርስ
ቅስም የሚያነኳኩት፣ ቅስም የሚገነባ፣ ሰብእና የሚያድስ
የትግል ማህጸን ጸንሶ ያፈራው፣ ዘላለማዊ ቅርስ።

ትንሽቱ አድዋ፣ ኢምንቲቱ ጭንጫ፣ አፍሪካዊት መሬት
ለኮሰች ነበልባል፤ ካለም ጫፍ የሚታይ እቶናዊ ሀውልት
የእሳት አምድ አቆመች፤ ጎልያድን ቢረታው ብላቴናው ዳዊት።
ልእልና ነስታ፣ ብኩርና ተሾመች፣ በድል ዙፋን መንበር
ፈነጠቀ ኮከብ፤ ከሰማይዋ ሰማይ፣ ከጠፈሯ ጠፈር
ከሩቅ እንዲጠራ፣ ሰብአ ሰገሎቿን ከእስያ ምድር።

የብርሃን ጎህ ቀደደ፣ የነጻነት ማሾ በራ
ህዝቦች የተሰዉለት የትግል ፍሬ ጎመራ።
እነሆ ከአምባሽ ግርጌ፣ ተሰየምን ከቅጥርሽ
ምእት አመት ተቀበልን፣ ዳግም ልንኮራ በስምሽ
እኛን ባንቺ ልናስተውል፣ በንስሃ ቃል ቀረብንሽ።

ለክብርሽ ዝክር ለመቆም፣ አቅም ሳይኖረው አቅማችን
ሚዛኑ ላይ እንደሚቀል፣ ገጸ በረከት፣ ስጦታችን
በመሰዊያው ላይ ኮስሶ፣ እንደሚያሳጣን መስዋእታችን
እየፈራን፣ እየሰጋን እያወቀው ልቦናችን፤
በጮራራ፣ በቀራራ፣ በኮሳሳ ተዳፈርንሽ
በራቀን ፍሬ ተስፋ ቆርጠን በደረስንበት ቀረብንሽ
ያበደርሽንን ውድ መክሊት ሳናተርፍበት ቆየንሽ።
ይቅር በይን አድዋ አንቺ የድል ጣኦታችን
የነጻነት ፈለግ ማሾ፣ የአድማስ ጫፍ እሳታችን
የማታልፊ፣ የማትከስሚ፣ የማትሞቺ ጀንበራችን
ያሻራ ማህተማችን፣ የግንባር ሽንተረራችን፣ የሰብእና ዋቢያችን
ባናክልም ያንቺን መጠን፣ ባንገዝፍም እንዳንቺ ግዝፈት
ሙሉ ነውና ልባችን፣ በፍቅርና በእምነት
አንድ ጧፍ እያነደደ፣ ያቆየ የወኔ ግለት
ክፉ ቀኑን የታገለ፣ በገድልሽ አርአያነት
ስምሽን እያዘመረ የኖረ ለሙቶ አመት፣

እባክሽን ተለመኚው፣ ዛሬም ጾም ያክፍልበት
በመንፈስ እየተበራታ፣ አካል ጉልበቱን ያድክምበት
ቀን ከሌት እየተራበ፣ ሽንብራ ይቆርጥምበት
በመረገሜሽ ይስገድበት፣ ስምሽን ጠርቶ ይማልበት
ሁሌም ለዝንት አለም ለነጻነት ይጣርበት።

ትናንት ህይወቱን እንደኖረበት፣ ተከትሎ ያንቺን ፋና
ነጻነቱን እንዳገኛት፣ ከእሾህ ከቆንጥር ጎዳና
እስቲ ዛሬም ይፈልጋት፣ ለስምሽ ሰጥቶ አዲስ ቃና
ሃይለኛ ማስገበሩን፣ ጉልበተኛ መናጠቁን፣ መቼም አይተውምና።

እንደማይመከት ልል ጋሻ፣ እንደማይደግፍ ሊጋ ባላ
ለወግና ለጌጥ እንጂ፣ ለሙቀት እንደማይለብሱት፣ ጥበብ ኩታ ነጠላ
አፍሪካዊ አርነቱ፣ አለባትና ሰሀ፣ ከጨረርዋ ጋር አይነ ጥላ
የታሪኩም ልቦናዋ ኢጋም ቀጋ፣ ቆንጥር እሾህ አሜኬላ
ያውሬ ማደሪያ ጭፍቅ ጫካ፣ አይነ ብርሀን ያሚከላ፣
ሆነበት መደናገሩን፣ አስተውዪው መፍረምረሙን
በጣላቸው አጥቂዎቹ፣ ስውር የግዞት ስራይ፣ በጀ ሰብእ መታሰሩን።

አስተውለሽ ይቅር በዪው
የዋህ ዝንጉ እንጂ፣ እርኩስ አይደለምና
አድሮ ጥጃ በመሆኑ ውስ! ብለሽ ኣታባሪው
የማደግ ተስፋውን ይልቅ በጠበልሽ አለምልሚው፤
በእጁ መሆኑን ንገሪው፣ ይህ ገድልሽ የተሰራው
ከድንዛዜው ቀስቅሰሽ፣ ከአዚም ባህር መንቂይው፤
አሳዪው ትንሳኤ ፋና፤ ንስሀ ፈልጓልና።
እባክሽን ተለመኚው፣ ዘንድሮም እንዳምና ሁኚው
የድል ጣኦትነትሽን፣ የነጻነት ብርሀንሽን፣ በቸርነትሽ ለግሽው።

በልቦናሽ ፈቃድ ይኑር፤ ይህ ነው ጉዱ ፈተናው
የአፍሪካዊ እጣ ፈንታ የክፍለ ዘመን ንስሀው፤
ታጥፋ ያልቀረች ስህተቱ፣ እሬት መራራ ጥፋቱ

ባድማ ከቀረች ልቡ፣ ወና ከሆነች ሰውነቱ
መኾሮር ተባይ፣ ነቀዝ ተባይ፣ በራሱ ላይ ማበጀቱ፤
በደም ውስጥ ሆና ስትጮህ፤ ባህር የምትንጥ ሀጢያቱ
አህጉር የምታናጋ፣ ሰብእናን የከረፋች ከፋቱ
እጁን በጁ የበላበት፣ ቃየላዊ ምግባሩ፣ የብብት እሳት ጸጸቱ።
ይህ ነው ጉዱ፣ ፈተናው፣ የንስሀ ሰበቡ
አውራ እንዳጣ መንጋ ንብ፤ ቀልቡን አጥቶ መዋከቡ፤
አቅል አስጥሎ የሚያካልብ፣ ባእድ ራእይ ተውሶ
እብድ እንዳየው ገበያ፣ በተምታቶት ተተራምሶ
የማያወዛ ተቀብቶ
የማያጠረቃ በልቶ
ሀሞት ቅስሙን መሻሽሩ፣ ልቦናውን ማላሸቁ
በነጻነቱ መደብ ጓዳ፣ የጣእር ጩኸት መስበቁ
የጎበጠ ደረቅ ልሳን
የሰለለ ደቂቅ ድርሳን
በምጿት እንጉርጉሮ፣ በርጥባን ዜማ ማረቁ፤

የፍቅርን ቆሌ ረብሿት፣ ማሳደዱ፣ ማብረሩ
በገዛ ኑሮው እንቆቅልሽ፣ ተተብትቦ መታሰሩ፤
በአዚሙ ክበብ ዙሪያ፣ እንደ ጨቅላ ተፍረምርሞ
በነጻነት አቀርቅሮ፣ ባገም ጠቀም ተፍገምግሞ
በሳቅ ለቅሶ ሲነፋረቅ
በለቅሶ ሳቅ ሲንሰቀሰቅ
በመጽዋቾቹ ማቅ ስላቅ፣ ኩራት እራቱ ስትማቅቅ፤
በመሆን ወይም ባለመሆን፣ በቁርጥ እውነት ሸምቀቆ
እየኖረ ባለመኖር፣ በህይወት አያዎ ታንቆ፤
የስርየቱ ቀን መርዘሙ፣ የምሬት ጽዋው መምረሩ
የጊዜ ዱካ መራቁ፣ ዘመን አልፎ መቆጠሩ
ይህ ነው ፈተናው ሀጢያቱ፣ የንስሀ ምስጢሩ።

ለታሪክማ ብኩርና፣ ለእውነታው ትልቅነት
ለአፍሪቃዊ አንጋፋነት፣ አዳማዊ አባትነት፤
አልፋ ኦሜጋ የታለ፤
ስብእና መች ሆነና፣ በቃል ሀጢያት የተቃለ
ተቅሎ የተቀጠለ፣ ጭንጫ ላይ የተበተነ፣ ከብዶ የተቃለለ
በሰዋሰው ተወሳውሶ በፊደል የተፈደለ
በመንጎል ጫፍ ተመንጉሎ፣ ሲፈጠር የተገደለ
ሲገደል የተፈጠረ፣ ነፍስ እስትንፋስ የታደለ።

እና፤ አድዋ! አንቺ በኩር የድል መከር
የቅኝ ግዛት ቀንበሩ፣ ሰንሰለቱ እንዲሰበር
ተጠቂዎች ካጥናፍ አጥናፍ የመረጡሽ የትግል ዘር
ህይወት ከፍለው እልፍ ያረጉሽ ያመረቱሽ ካገር አገር
የማታልፊ፣ የማትከስሚ፣የማትሞቺ ህያው ጀንበር
ስብአዊ ድል ነሽና ስምሽ ይወደስ ይዘመር።
በህያላን የተጠቁ
በባርነት የማቀቁ
ቃላቸውን ያጸኑብሽ፣ ቀድመው የጠጡሽ ጽዋ
ወኔያቸውን ያነሳሳሽ፣ የትግል ደወል መረዋ
የድል፣ የፍትህ ጣኦት አፍሪካዊቱ አድዋ፤
እነሆ ታሪክ ተጉዞ ምእተ አመተ አከለ
ሃያል ልሳን ተሰማ፣ ከልሳን ሁሉ ያየለ።
አህጉራትን ዘልቆ
ውበትን ህብረ ዝማሬ በጠፈርሽ ላይ አዋለ
አገር አመሰገነ፣ ቃለ መወድስ ከፈለ።

አድዋ! አንቺ የድላችን ጣኦት
መገን! ለሁነትሽ ታምር ሁነት
አቤት! ለመከዳሽ ክቡር ክብረት
ለዙፋንሽ ሰብእና፣ ለሰብእናው ልእልና፣
ለምጥቀቱ ምጡቅ ምጥቀት
መገን! ለቆምሽበት ጥቁር አፈር፣ ለበቀልሽበት ሰናይ አለት
የሰብእና ሃሌታ ጡብ መሰረቱ ላረፈበት፤
በአዳም እግሮች ለተሟሸው፣ ለኢትዮጵያ ጭንጫ መሬት
ታሪክ መሆንን ሆኖ እትብቱ ለወደቀበት
አቤት አድዋ! አቤት...አቤት...

አገር አመሰገነ፣ ቃል መወድስ ከፈለ
ደጀ ሰላምሽን ሞልቶ፣ በስብሳብሽ ተጠለለ፤
አፍሪካዊና እስያዊ ለምኩራብሽ ተሰይሞ
በነፍሱ የቋጠራትን የታሪክ ኪዳኑን ደግሞ።
ካጥቂና ከነጣቂ ጋር
ከሲላና ከተኩላ ጋር
የታገለውን ትግሉን በልቦናው አስታመመ
በድሉ ትውስታ መጥቆ፣ በትልቁ ባህር ሰጠመ
በኪዳንሽ መዝሙር ዜማ፣ አገር ማህሌት ቆመ
በዝማሬ ሰረገላ፣ በቅኔ ክንፍ በረረ
የመቶ አመት ርቀቱ፣ የዘመን ኬላ ተሰበረ
የታሪክ ምስጢር ገበና፣ ካዝናው ተበረበረ።

## የአድዋ መቶ ሶስተኛ አመት

ከአድዋ ምእት አመት ይልቅ መቶ ሶስተኛው በአል በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል። ዋናው ምክንያት ቅጥ ባጣው የወንድማማቾች ጦርነት ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር የነበራትን ጦርነት በድል ማጠናቀቋ ጋር የተያያዘ ሲሆን መንግስትም የመቶኛውን አመት አይነት ቸልተኝነት ሳያሳይ ህዝቡም ሆ ብሎ ወጥቶ ደስታውን ገልጿል። አንዱ ግጥም (ቢኒያም 1997፡98) ይህን ይመስላል።

መቶ ሶስት አመት ተጉዘሽ
ዛሬ ከእኛ ስትደርሽ
ወጉ ደርሶን.. ልጆችሽ
አንብድደን አይደለም...የጠበቅንሽ
...
የሚያስተውል...ከአድዋ...አሻግሮ
በባድመ በሽራሮ

ድህረ አድዋ የኪነጥበብ መወድሶች የሀይሌ ገሪማ "አድዋ የአፍሪካ ድል" (1999) ፊልምና ለፊልሙም ማጀቢያ ጂጂ (እጅጋየሁ ሽባባው) ያቀነቀነችው አድዋ የተሰኘው ዘፈን ሳይጠቀሱ አይታለፉም። የዘንድሮ የመቶ አስራ አራተኛ አመት ዝክረ አድዋ ቢያንስ በሰሜን አሜሪካ በተለያዩ ዝግጅቶች እየታሰበ ነው። ከመገናኛ ብዙኃን ዘገባዎች እይታ አንጻር የሚኒሶታው ዝግጅት የሚደምቅ ይመስላል።

**ቸር እንሰንብት !**

## የግርጌ ማስታወሻዎች


1. "...ዘመን"፤ "...ዘመን"፤ "...ዘመን" እውቁ ሳህለስላሴ ብርሃነ ማርያም በባሻ ቅጣው መጽሀፋቸው ውስጥ የተጠቀሙበት የግጥምጥምነት ዘይቤ

2.ተስፋዬ ገሰሰ፡፡1980። አኮቴት ለከበደ ሚካኤል "እሮሮ"፡፡ ያልታተመ ጽሁፍ።

3. ባዩ በየነ።2000። ፍቅር ወይስ ቂጣ በ«አቦል» መድበለ ግጥምና አጫጭር ጽሁፎች። ቶሮንቶ፤ ሐዲስ የኪነ ጥበባት መድረክ። ገጽ 135-137።

4. ባዩ በየነ።2000። አበሳሽን እኖራለሁ በ«አቦል» መድበለ ግጥምና አጫጭር ጽሁፎች። ቶሮንቶ፤ ሐዲስ የኪነ ጥበባት መድረክ። ገጽ 138-145።

5. ታምራት ገበየሁ።2000። የማስቸግራችሁ በ«አቦል» መድበለ ግጥምና አጫጭር ጽሁፎች። ቶሮንቶ፤ ሐዲስ የኪነ ጥበባት መድረክ። ገጽ 202።

6. ዮሴፍ ያእቆብ ።2000። ነፍስ በ«አቦል» መድበለ ግጥምና አጫጭር ጽሁፎች። ቶሮንቶ፤ ሐዲስ የኪነ ጥበባት መድረክ። ገጽ 225-6።

7.በዕውቀቱ ስዩም። 2001። ስብስብ ግጥሞች። አዲስ አበባ፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ።

8. አሉላ ዋሴ (ዶ/ር)። ወደ ጦር ሜዳ። http://eedn.org/resources/ethnocentrism_%20partIII.pdf downloaded on February 25,2010.

9. ተስፋዬ ገሰሰ፡፡1980። አኮቴት ለከበደ ሚካኤል "እሮሮ"፡፡ ያልታተመ ጽሁፍ።

10. Biniam Weldegebreil.2004 (1997). Memories of the victory of Adwa: A focus on its commemoration (1941-1999). Addis Ababa: Addis Ababa University. M.A. thesis.

11.http://www.abyssiniagateway.net/fidel/let/adwa-sera.html downloaded on February 25, 2010.